# ከሕዝብ ጀርባ የሚሸረብ ሴራ ሁሉ መጋለጡ አይቀርም

የነገሮችን ውሀ ልክ ወይም ውል ያጡ ግልፅነት ሲባል ሰምተዋልና ወያኔን የመሰለ አረመኔ ጠላት ባለበት ሁሉም ግልፅ ሆኖ ይታየን ይቅረብልን ብለው ለጥራዝ ነጠቅነት ሲሰግዱ ወይም ሰለባ ሲሆኑ መታዘብ ተገደናል። በአንፃሩ ደግሞ ከሕዝብ በስተጀርባ በተለይም ከባዕዳን ጋር ሴራ መሸረብ የለመደባቸው እንዳሉ የሕዝብን ትግል ከባዕድ ኤምባሲ ሀላፊዎች ጋር በመሆን ያከሸፉትን በምሳሌነት በመጥቀስ ለመረዳት ይቻላል።

ድርጅቶች ትግሉን ከግብ ለማድረስ ከተነሱ ብዙ ምስጢራቸውን ከጠላት ዓይን ሰውረው መያዝ መቻል አለባቸው። በውስጣቸው ጠላት ሰርጎ ሊገባም ስለሚች ልም ምስጢር የባቄላ ወፍጮ አለመሆኑን ማወቅና በስራ መዋልም ይጠበቅባቸ ዋል። ሰርጎ ገቦች አንዱ መለያቸው በአባል ነን ሽፋን የማይመለከታቸውን ሁሉ ለማወቅ ሲያነፈንፉ መታየታቸው ነው። እንኳን በትግል ላይ ያለ ሀይል ቀርቶ ኀያላን ነን ብለው በዓለም ላይ የተሰየሙት እነ አሜሪካ ራሳቸው ብዙውን ተል ዕኮአቸውን በመስጢር ይዘው እየታወቀ ግልፅነት የተባለውን በግልቡ በመያዝ ሁሉም ይጋለጥ ይታወቅ ብለው የሚለፍፉት ወደዱም ጠሉም ለጠላት ለወያኔ መጥቀማቸው አከራካሪ አይደለም። ድርጅቶች በህጋዊነት ተመዝግበዋል ስለተባለም ምስጢር የላቸውም ማለት አይደለም። ለጠላት ክፍት ሆኖ መገኘት --ያውም ጠላት የራሱን ብዙ ምስጢር ደብቆ ይዞ ባለበት--በራስ ላይ ሞትንና ውድቀትን መፍረድ ነው። በዚሁ ልክ ደግሞ የምስጢር ዲፕሎማሲ እንዳለ ግልፅ ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶች ይቅርና መንግስታትም በምስጢር የሚይዟቸ ው ግንኙነቶች አሉ። በዚህ ላይ ብዙ ጠብ አይኖርም። ዋናው ቁምነገር ግን ከሕዝብ በስተጀርባ የሕዝብን ትግል በሚጎዳ መልኩ የሚደረጉ ድርድሮችና ስምምነቶችን ይመለከታል። ከወያኔ ጋር ተፃረን ቆመናል እየተባለ ከአገዛዙ ጋር በምስጢር ተደራድሮ በሕዝብ ትግል ላይ ደባ መፈፀም ለምሳሌ ወንጀል ሊባል የሚገባው ነው። ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ ያ ሁሉ ደም ፈሶ የሙት ከተማ አድማ ሲዘጋጅ ይህንኑ ታሪካዊ ሊሆን ይችል የነበረን አድማ ከአሜሪካን ኤም ባሲ ተጠሪ ከነበረች ፀረ ኢትዮጵያ ግለሰብ ጋር ሁለት የተቃዋሚ ስብስቦች መሪዎች ነን የሚሉ በምስጢር ተደራድረውና ተስማምተው አክሽፈውታል። ምን ተነጋገሩ?ምን ተስማሙ? የማወቅ መብት ያለው ሕዝብ እስከዛሬ ስለ ጉዳዩ የሚያውቀው ዝርዝር የለም። የወያኔ አገዛዝ እያወቀው ግን ይኸው ጉዳይ ዝርዝሩ ከሕዝብ ሲደበቅ የተበላሸ ነገር መኖሩን ለማወቅ አያዳግትም። ምስጢሩ ለጠላት ተነግሮ እንዴት ከሕዝብ ይደበቃል? በቃሊቲ የታሰሩትን የተ ቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ልናስፈታ ነው በሚል ለአገዛዙ ድጋፋቸውን ያልካዱ አስታራቂ ተብዬዎች ይንቀሳቀሱ በነበረበት ጊዜ ሂደቱን መለስ ዜናዊ በዝርዝ ር ሲያውቀው ለሕዝብ ግን ግልፅ አልነበረም። ከዚህ ሁሉ ቀደም ብሎ ደግሞ ራሱን ኢዴፓ ብሎ የሰየመ ቡድን የመሪዎቹን ስም ዝርዝር ለወያኔ አቅርቦ እያለ እነ እገሌ መሪዎቹ ናቸው በመባሉና ለሕዝብ በመነገሩ ያሰማውን ኡኡታ አንረሳም።ይኸው ኢዴፓ ከወያኔ በምስጢር ተደራድሮ ቅንጅቱን ተፃሮ በወያኔ ፓርላማ መግሸባቱ ሲታወስ የኢዴፓን መሪዎች ነን ያሉ ግለሰቦችም ከድርጅ ታቸው ተደብቀው ከወያኔ ተደራድረው ወደ ወያኔ ፓርላማ ገብተዋል።

በተለምዶ አነጋገር ክህደት ፈፅመዋል።

በአሁኑ ጊዜ በሕዝብ ትግል ላይ ልዩ ልዩ ሴራዎች ተሸርበው ተግባራዊ ሊሆኑ ደፋ ቀና እያሉ ናቸው። በመጪው የወያኔ የምርጫ ቧልት አገዛዙ 4 ሚሊዮን ዕጩዎች አዘጋጅቻለሁ እያለ መሆኑን መጥቀስም አስፈላጊ ነው። ወያኔ የምር ጫው አሸናፊ ለመሆኑ ከዛሬው መናገር ቢቻልም ተወዳደረ ይባል ዘንድ ደግሞ አጃቢ ይፈልጋል። ይህን የትብያ ሚና ለመጫወት ደግሞ ራሳቸውን በይፋም በስውርም ያዘጋጁ ጥቂቶች አይደሉም። ለዘብተኛ ወይም ታማኝ ተቃዋሚ የሚል የሽፋን ስም ተዘጋጅቶላቸዋል። የሀገርና የህዝብ ዕጣ እየተወሰነ ያለበት ን የፖለቲካ ሂደት በቲያትር ደረጃ ወስደው ያሉ መድረክ አጣባቢዎች ደግሞ ሳያፍሩ ለዚህ የተለጣፊ ሚናቸው ብዙ ሚሊዮን ብር ሊሰጣቸው ቃል የገባ ባዕድ ሀገር መኖሩንም ነግረውናል። ከዚሁ ባዕድ ሀገርና በዚሁ ባዕድ ሀገርም የምስጢር ስብሰባዎች ሲካሄዱና ስምምነቶችም ሲደረጉ እንደነበርም ታውቋል፡ የተወሰኑ ሀይሎችን ለማጥላላትና ለማግለል፤ለመከፋፈልና ለማዳከም የተቀነባበረ ዘመቻ መከፈቱም ምስጢር አይደለም። ለሕዝብም ጀግናዎችህ እነ እገሌ ናቸው ተብሎ እየተነገረውና ለነገው የሴራው ክንውን አጨብጫቢና ተቀባይ ለማድረግ እንዲለምድ እየተደረገ ነው። ከሕዝብ ጀርባ እየተሰሩ ያሉትን ትግል ጎጂ ድርጊቶች ከግብ ለማድረስ የሕዝብን ብሩህ ተስፋ ማጨለ ምና ሽንፈተኛነትን ማስፈን ወሳኝና አስፈላጊ በመሆኑም ይህንንም ተያይዘው ታል። የወያኔ አገዛዝ አይበገርምና በፀጥታ ተገዙለት ብለው የሚሰብኩት እነ ፕሮፌሰር እገሌ ምሳሌ ናቸው። አሜሪካ ኀያል ሀገር ነውና ፤ ሊሰገድለት ይገባልና ስርየታችንን ከጫማው ስር ወድቀን እንለምን--- እንጠብቅ የሚሉን ስልጡን ፖለቲከኞች ደግሞ ሌላ ምሳሌ ናቸው። የወያኔ አገዛዝን ተልዕኮ ሊያሟሉ ወዲያ ወዲህ ከሚሉት ግለሰቦች ጋር በድብቅ የሚሰበሰቡትም አላረፉም። ለወያኔው የፀጥታ ሀላፊ ለጌታቸው አሰፋ እየደወሉ ዘገባና መረጃ አቅራቢዎች ደግሞ በይፋ ራሳቸውን ተቃዋሚ ብለው ሰይመው እንደሚያደናግሩ ያልታወቀ ነገር አይለደም።

ለዚህም ነው ከሕዝብ ጀርባ የሚሸረብ ሴራ በሞላ ሳይውል ሳያድር ይጋለጣል የምንለው። የሕዝብ ዓይን በሚሊዮን ነው፤ጆሮዎቹም እንዲሁ። ከወያኔ ሆነ ከባዕዳን ጋር በተዘጋ ክፍል የሚደረጉ ስምምነቶች ይጋለጣሉ። ሰነዶቹ ይወጣሉ ፤ ሕዝብም ግልፅ ይደረጋሉ። በዚህም መንገድ ሴራዎቹ ተጋልጠው በእንጭጩ ይከሽፋሉ ወይም ሕዝብ አውቆ ይታገላቸዋል። ለሕዝብ ማሳወቅና ሕዝብን ማዘጋጀት ደግሞ የሀቀኛ ሕዝባዊ ድርጅቶች ግዳጅ ነው። በመጪው ምርጫ አገዛዙን ለማጀብ ከወዲሁ ላይ ታች ማለቱ መጀመሩንና ይህ ደግሞ የሚፈይደው ዜሮን ብቻ መሆኑን ማጋለጥ ተገቢ ነው። መለስ ዜናዊ ተቀይሯል የሚለውን የሀሰት ቅስቀሳንም እንዲሁ አዎ ከእባብ ዕንቁላል ርግብ ተወልዳለ ች በሚል ደረጃ “መቀበል” ያለብን መሆኑንም መግለፅ እንገደዳለን። የወያኔ አገዛዝን ጠላት ነው ማለት ያልሰለጠነ ፖለቲካ ነው ሲሉንም እሰየው ባንሰለጥን ይቅር ለማለት ድፍረቱ ሊኖረን ይገባል ማለት ነው። በሰላማዊ ትግል አባወራነት ሽፋን ለወያኔ አገዛዝ እጅ መስጠትን የሚሰብኩትንም እምቢኝ

ማለት የዜጋ ግዴታችን መሆኑን ማስረዳት ይገባናል። ከወያኔ አገዛዝና ከባዕዳን ጋር በድብቅ ሴራ ጉንጎናው ያለና የቀጠለ ነው። ይህ ሁሉ ግን መጨረሻው ውድቅ ነው። የወያኔ አገዛዝ ተለጣፊዎች፣ የባዕዳን ሀገር ሎሌዎች ሁሉም ይጋለጣሉ፣ ከሕዝብ ጀርባ የሚዶለተው ሁሉ ይከሽፋል። ከወያኔ አገዛዝና ከመሰሎቹ ጋር የሚተቃቀፉት ሁሉ ተለጣፊነታቸው ምስጢር ሆኖ አይቀርም። አንጃ ግራንጃ፣ ተለጣፊ አነፍናፊ፣ ቅጥረኛ ማፈሪያ ሁሉም ይጋለጣል። የኢትዮጵያ ሕዝብም አቸናፊነት ይረጋገጣል።